# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁ. 235844

ጥቅምት 06 ቀን 2016 ዓ.ም

**ዳኞች፡-**

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

እንዳሻዉ አዳነ

ተሾመ ሽፈራዉ

መላኩ ካሳዬ

ነፃነት ተገኝ

**አመልካች፡** ዙበይዳ መሐመድ

**ተጠሪዎች፡**

1. አቶ ቶፊቅ አብደላ
2. ወ/ሮ ለይላ አብደላ
3. ወ/ሪት አሚና አብደላ
4. አቶ አብዱልሃፊዝ አብደላ
5. ወ/ሮ አዲስ አብደላ
6. አቶ ዳዊት አብደላ
7. አቶ አይከል አብደላ
8. አቶ ተይሰር አብደላ

ከ1ኛ እስከ 5ኛ ተጠሪዎች እንዲሁም ከ6ኛ እስከ 8ኛ ተጠሪዎች ያቀረቡትን መስቀለኛ የሰበር አቤቱታን አስመልክቶ ተከታዩ ትዕዛዝ ተሰጥቷል፡፡

**<u>ትዕዛዝ</u>**

መስቀለኛ የሰበር አቤቱታዉ የቀረበዉ በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ 01 የቤት ቁጥር አዲስ የካ/ቁጥር 112/309/00 አስመልክቶ የስር ፍርድ ቤት የሰጠዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆኑን በመጥቀስ ቢሆንም፣ መስቀለኛ የሰበር አቤቱታ አቅራቢዎች ከዚህ ጋር በተያያዘ ይግባኝ ወይም የመስቀለኛ ይግባን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ማቅረባቸዉን የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ አያሳይም፡፡ ስለሆነም መስቀለኛ የሰበር አመልካቾች (ተጠሪዎች) ለመስቀለኛ የሰበር አቤቱታቸዉ መሠረት ካደረጉት ንብረት ጋር በተያያዘ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በሰጠዉ ዉሳኔ ላይ ቅሬታ ካላቸዉ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበዉ እንዲታረምላቸዉ ሳይጠይቁ በቀጥታ ለዚህ ሰበር ያቀረቡት አቤቱታ፣ አንድ ጉዳይ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቀርቦ ሊታይ የሚችልበትን ሁኔታ አስመልክቶ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10(1-ሀ) ላይ የተመለከተዉን ድንጋጌ ያላገናዘበ በመሆኑ ተቀባይነት የለዉም፡፡

**የሰ/መ/ቁ.** 235844

ጥቅምት 06 ቀን 2016 ዓ.ም

**ዳኞች፡-**

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

እንዳሻዉ አዳነ

ተሾመ ሽፈራዉ

መላኩ ካሳዬ

ነፃነት ተገኝ

**አመልካች፡** ዙበይዳ መሐመድ

**ተጠሪዎች፡**

1. አቶ ቶፊቅ አብደላ
2. ወ/ሮ ለይላ አብደላ
3. ወ/ሪት አሚና አብደላ
4. አቶ አብዱልሃፊዝ አብደላ
5. ወ/ሮ አዲስ አብደላ
6. አቶ ዳዊት አብደላ

*ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

7. አቶ አይከል አብደላ
8. አቶ ተይሰር አብደላ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የአሁን 1ኛ ተጠሪ፣ አመልካችን እና ከ2ኛ እስከ 5ኛ ያሉትን በተጠሪነት በመሰየም ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ባቀረበዉ አቤቱታ ታህሳስ 09 ቀን 2012 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩት የአባታቸዉ የአቶ አብደላ ሰርሞሎ የዉርስ ሀብት እንዲጣራ የጠየቀዉን ዳኝነት መነሻ ያደረገ ነዉ፡፡ ከ 6ኛ እስከ 8ኛ ተጠሪዎችም በክርክሩ ጣልቃ ገብተዋል፡፡ በዚህም መሠረት የሟች የዉርስ ሀብት ተጣርቶ ለፍርድ ቤቱ ቀርቧል፡፡ በቀረበዉ ሪፖርት ላይ ግራ ቀኝ አስተያየታቸዉን እንዲያቀርቡ ተደርጎ፣ በዚህም መሠረት ግራ ቀኝ በየበኩላቸዉ አስተያየታቸዉን አቅርበዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተዉ ፍርድ ቤትም የቀረበለትን የዉርስ አጣሪ ሪፖርት ከግራ ቀኝ ክርክር እና ማስረጃ አንፃር ከመረመረ በኋላ፤ የቤት ቁጥር አዲስ ሆኖ በኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ ወረዳ 02 ዉስጥ የሚገኘዉ ቤት የተፈራዉ ከሟች ጋር ከመጋባታችን በፊት ነዉ በማለት አመልካች የምትከራከር ቢሆንም፣ ሟች እና አመልካች በጋብቻ እያሉ ቤቱን የጋራ አድርገዉ በስማቸዉም ተመዝግቦ ካርታ የተሰጣቸዉ መሆኑ በመረጋገጡ እና በፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 1195 መሠረት የባለቤትነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰጠዉ ሰዉ የንብረቱ ባለቤት ሲሆን ይህን የሚያስተባብል ማስረጃ አመልካች ያላቀረቡ በመሆኑ ቤቱ የጋራ ነዉ፡፡ በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 05 የቤት ቁጥር 173 አስመልክቶ አመልካች ቤቱ የሟች የነበረ ቢሆንም፣ ከተጋባን በኋላ የጋራችን እንዲሆን ተስማምተናል የሚል ክርክር ያቀረቡ ቢሆንም ይህን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ያላቀረቡ በመሆኑ ክርክራቸዉ ተቀባይነት የለዉም፡፡ በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ 01 የካ/ቁጥር 112/509/00 የሆነዉ ቤት ከጋብቻ በፊት የተፈራ የአመልካች የግል ንብረት መሆኑ መረጋገጡን ጠቅሶ፣ ይህ ቤት የሟች ድርሻ እንዳለበት በመጥቀስ ተጠሪዎች ያቀረቡትን ክርክር ዉድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተዉ ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ይህንኑ ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበዉም በዚሁ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ሲሆን፣ አመልካች ጥቅምት 11 ቀን2015 ዓ.ም ጽፈዉ ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ የሚሉባቸዉን ምክንያቶች በመዘርዘር ታርሞ ይወሰንላቸዉ ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የሰበር አቤቱታቸዉ መሠረታዊ ይዘትም፤ በኮልፌ ቀራኒዮ ክ/ከተማ የቤት ቁጥር አዲስ የካርታ ቁጥር ወ2/ዉዝ01/1510/24129/00 የሆነዉ ቤት የተሰራዉ አመልካች ከሟች ጋር ትዳር ከመመስረታቸዉ በፊት ያፈሩት ስለመሆኑ ተረጋግጦ እያለ እና ሟች ያደረገዉ አስተዋጽዖ ሳይኖር የስር ፍርድ ቤት የጋራ ነዉ በሚል መወሰኑ፤ እንዲሁም በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 5 የቤት ቁጥር 173 ያለዉ ንግድ ቤት ከሟች ጋር የጋራ እንዲሆን ተስማምተን አከራይተን በጋራ ስንጠቀምበት የነበረ ሲሆን፣ ስመ ሀብቱ በሟች ስም ስለሆነ ብቻ የጋራ አይደለም በማለት መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት ነዉ የሚል ነዉ፡፡

የሰበር አቤቱታዉ በአጣሪ ችሎት ተመርምሮም መኖሪያ ቤቱ ሟች እና አመልካች በትዳር እያሉ በጋራ ያፈሩት መሆን አለመሆኑ በጭብጥነት ተይዞ ሳይመረመር፣ የትዳር ተጋሪ በሚል የሟች ስም በባለይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ላይ በመመዝገቡ ብቻ የጋራ ነዉ በሚል የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡትን ዉሳኔ አግባብነት ግራ ቀኝ በተገኙበት አጣርቶ ለመወሰን ሲባል ያስቀርባል ተብሏል፡፡ በዚህም መሠረት ከ1ኛ እስከ 5ኛ ተጠሪዎች ሚያዝያ 16 ቀን 2015 ዓ.ም አዘጋጅተዉ ያቀረቡት መልስ ይዘት

ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በአጭሩ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ቤት የጋራ መሆን አለመሆኑን ጭብጥ አስይዘዉ ሳይከራከሩ ይህን አስመልክቶ ያቀረቡት ክርክር ከፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 329 አንፃር አዲስ ክርክር ከመሆኑም በላይ ቤቱ የጋራ መሆኑ ተረጋግጦ በዉርስ አጣሪዉ የቀረበዉን ሪፖርት በማጽደቅ የስር ፍርድ ቤት የሰጠዉ ዉሳኔ ተቀባይነት የለዉም፡፡ አመልካች እና ሟች በትዳር አብረዉ ሲኖሩ ቤቱ የጋራቸዉ እንዲሆን ተማምነዉ ጉዳዩ በሚመለከተዉ የመንግስት ተቋም ተጣርቶ የጋራ ባለ ሀብቶች መሆናቸዉን የሚያረጋግጥ የይዞታ ማረጋገጫ የሰጣቸዉ ሲሆን ይህም ማስረጃ በፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 1195 መሠረት የጋራቸዉ ስለመሆኑ ግምት የሚወሰድበት ሲሆን፣ ይህን ግምት የሚያስተባብል ማስረጃ አመልካች አላቀረቡም፡፡ በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ዉስጥ ያለዉ ንግድ ቤት የተጠሪዎች አባት የግል ንብረት ነዉ የተባለበት ምክንያት ጋብቻ ከመፈጸሙ በፊት የተሰራ መሆኑ በመረጋገጡ ነዉ፡፡ በመሆኑም የአመልካች ክርክር ዉድቅ ይደረግልን በማለት ተከራክረዋል፡፡ ከ6ኛ እስከ 8ኛ ያሉት ተጠሪዎችም መጋቢት 26 ቀን 2015 ዓ.ም የተፃፈ ከ1ኛ እስከ 5ኛ ተጠሪዎች ካቀረቡት መልስ ጋር ተመሳሳይ ይዘት ያለዉ መልስ አቅርበዉ ተከራክረዋል፡፡ አመልካች ሚያዝያ 30 ቀን 2015 ዓ.ም ባቀረቡት የመልስ መልስ የሰበር አቤቱታቸዉን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

ከስር ጀምሮ የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኝ ክርክር ይዘት አጠር አጠር ባለ መልኩ ከፍ ሲል የተመለከተዉን ሲመስል፣ ይህ ችሎትም የሰበር አቤቱታዉን ለማስቀረብ የተያዘዉን ጭብጥ ከግራ ቀኝ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረዉም አመልካች ለዚህ ሰበር ባቀረቡት አቤቱታ አጥብቀዉ የሚከራከሩት እና በሰበር አጣሪ ችሎትም የተያዘዉ ጭብጥ በኮልፌ ቀራኒዮ ክ/ከተማ የቤት ቁጥር አዲስ የካርታ ቁጥር ወ2/ዉዝ01/1510/24129/00 የሆነዉን ቤት አስመልክቶ የተሰጠ ዉሳኔን የሚመለከት ነዉ፡፡ ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ እንደሚቻለዉ አመልካች በዚህ ረገድ የሚከራከሩት ቤቱን አመልካች ከሟች (የተጠሪዎች አባት) ጋር ጋብቻ ከመመስረታቸዉ በፊት በ1988 ዓ.ም በተደረገ ዉል ከእነ ሻምበል በቀለ ዳዲ የገዙ መሆኑን በመጥቀስ ነዉ፡፡ አመልካች ይህን ክርክራቸዉን ለዉርስ አጣሪ ጭምር ያቀረቡ ቢሆንም፣ ዉርስ አጣሪዉ ቤቱ በአመልካች እና በሟች (በተጠሪዎች አባት) ተመዝግቦ የሚታወቅ መሆኑን ጠቅሶ የሟች ድርሻ አለበት የሚል በሪፖርቱ አካቷል፡፡ አመልካች የዉርስ ሪፖርቱ ከመጽደቁ በፊት ለፍርድ ቤቱ ባቀረቡት አስተያየትም ይህንኑ ክርክራቸዉን ያቀረቡ ሲሆን፣ ተጠሪዎች በበኩላቸዉ ለቤቱ ካርታ የተሰራዉ በ2002 ዓ.ም መሆኑን ጠቅሰዉ ቤቱ የሟችና የአመልካች የጋራ ንብረት ነዉ በማለት መከራከራቸዉን የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ግልባጭ ያሳያል፡፡ ከዚህ ዉጪ ቤቱ የተገዛዉ አመልካች እና ሟች (የተጠሪዎች አባት) ጋብቻ ከመመስረታቸዉ በፊት በ1988 ዓ.ም ነዉ በሚል አመልካች ያቀረቡትን ግልጽ ክርክር ተጠሪዎች ክደዉ አልተከራከሩም፡፡ ለዚህ ሰበር ባቀረቡት መልስም ይህን በግልጽ ክደዉ አይከራከሩም፡፡ ተጠሪዎች በዉርስ አጣሪ እንዲሁም በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ለቀረበባቸዉ ይግባኝ በሰጡት መልስ፣ ቤቱ የተሰራዉ በሟች የግል ንብረት በተገኘ ገቢ ነዉ የሚል ክርክር አንስተዋል፡፡ ይሁንና ቤቱ የተገዛዉ በ1988 መሆኑ በግልጽ እስካልተካደ ድረስ ከጋብቻ በፊት የነበረ ቤት እንደሆነ የሚገመት በመሆኑ፣ አመልካቾች ቤቱ የተገዛዉ ከጋብቻ በፊት ነዉ በሚል የቀረበዉን ክርክር በግልጽ ባልካዱበት ሁኔታ በሟች የግል ንብረት የተሰራ ነዉ በማለት የሚያቀርቡት ክርክር ተቀባይነት ያለዉ አይደለም፡፡

ከላይ እንደተገለጸዉ የስር ሁለቱ ፍርድ ቤቶች ቤቱ የጋራ ነዉ በሚል ድምዳሜ ላይ የደረሱት በሟች እና በአመልካች ስም ተመዝግቦ የሚታወቅ በመሆኑ በፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 1195 መሠረት የሟች እና የአመልካች የጋራ ንብረት እንደሆነ የሚገመት መሆኑን በመጥቀስ ነዉ፡፡ በርግጥም በፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 1195 ላይ እንደተመለከተዉ የማይንቀሳቀስ ንብረት በስሙ የተመዘገበ ሰዉ የንብረቱ ባለቤት እንደሆነ

ይገመታል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ ጀርባ ያለዉ መሠረተ ሃሳብም የማይንቀሳቀስ ንብረትን አስመልክቶ የባለቤትነት ማረጋገጫ ማስረጃ (የምስክር ወረቀት) የሚሰጥ የአስተዳደር አካል፣ ማስረጃዉን ከመስጠቱ በፊት፣ በርግጥም የባለቤትነት ማረጋገጫ ማስረጃ የተሰጠዉ ሰዉ በማስረጃዉ ላይ የተመለከተዉ ንብረት ባለቤት መሆኑን ህግና ሥርዓትን ተከትሎ በተጠያቂነት እና በኃላፊነት መንፈስ በአግባቡ አጣርቶ ይሰጣል ተብሎ ስለሚታመን መሆኑን ከህጉ አንቀስ 1195 እንዲሁም ከማይንቀሳቀስ ንብረት ምዝገባ ጋር በተያያዘ በህጉ አንቀጽ 1553 እና ተከታዮቹ ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ መገንዘብ ይቻላል፡፡ የማይንቀሳቀስ ንብረትን አስመልክቶ የሚሰጥ የባለቤትነት ማረጋገጫ ማስረጃ (የምሰክር ወረቀት)፣ ስሙም እንደሚያሳዉ፣ በህግ ለተቋቋመን የባለቤትነት መብትን ለማረጋገጥ የሚሰጥ ማስረጃ እንጂ ብቻዉን የባለቤትነት መብትን የሚፈጥር አለመሆኑንም ልብ ማለት ያስፈልጋል፡፡

በሌላም በኩል የንብረት ባለቤትነት መብት በዓለማችን በተለያየ መልኩ በህግ ዕዉቅና ከተሰጣቸዉ የሰዉ ልጆች መብቶች መካከል አንደኛዉ መሠረታዊ መብት ነዉ፡፡ ይህ መብት የተባበሩት መንግስታት ቻርተር እ.ኤ.አ በ1945 ከወጣ በኋላ የመጀመሪያዉ የሆነዉ የሰብአዊ መብቶች ሁሉ አቀፍ መግለጫ እ.ኤ.አ በ1948 ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ በወጡ ዓለም አቀፍ፣ አህጉራዊና ብሔራዊ ሰብአዊ መብት ነክ ሰነዶች ተካቶ ይገኛል፡፡ የተባበሩት መንግስታት ያወጣዉ የሰብአዊ መብቶች ሁሉ አቀፍ መግለጫ (Universal Declaration of Human Rights) አንቀጽ 17 ማንም ሰዉ ብቻዉንም ሆነ ከሌሎች ጋር በመተባበር የንብረት ባለቤት የመሆን መብት ያለዉ መሆኑንና ማንም ሰዉ በዘፈቀደ ንብረቱን እንዲያጣ እንደማይደረግ ይደነግጋል፡፡ አህጉራዊ የሰብአዊ መብቶች ሰነዶች ከሆኑት መካከል በአፍርካ የሰዎችና የህዝቦች መብቶች ቻርተር ሰነድም የንብረት ባለቤት የመሆን መብት የህግ ዋስትና ያለዉ መሆኑን ይደነግጋል፡፡ ኢትዮጵያ ዋነኞቹን በሰብአዊ መብቶች ላይ ያተኮሩ አለም አቀፍ ሰነዶችን ያጸደቀች ከመሆኗም በላይ በህገ መንግስቷ ዉስጥ ዕዉቅና በመስጠት የአገሪቷ የህግ አካል አድርጋቸዋለች፡፡ በኢፌዲሪ ህገ መንግስት ማንኛዉም የኢትዮጵያ ዜጋ የግል ንብረት ባለቤት መሆኑ/መሆኗ እንደሚከበርለት/እንደሚከበርላት (Every Ethiopian citizen has the right to the ownership of private property) ሲደነግግ የንብረት ባለቤትነት ምንጭ ደግሞ አንድ ሰዉ በጉልበቱ፣ በመፍጠር ችሎታዉ ወይም በካፒታላቸዉ ያፈሩት (is produced by the labor, creativity, enterprise or capital of an individual) ሀብት ስለመሆኑ በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 40(1 እና 2) ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህ ድንጋጌ ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ተብለዉ ከሚታወቁት መብቶች ዉስጥ የሚገኝ በመሆኑ በማንኛዉም ደረጃ የሚገኙ የፌዴራል መንግስትና የክልል ህግ አዉጪ፣ ህግ አስፈፃሚ እና የዳኝነት አካሎች የማክበርና የማስከበር ኃላፊነትና ግዴታ ያለባቸዉ መሆኑን በአንቀጽ 13(1) በአስገዳጅነት ተደንግጓል፡፡ ስለሆነም ከንብረት መብቶች አተገባበር ጋር በተያያዘ ክርክር ሲኖር፣ ፍርድ ቤቶች በተቻላቸዉ መጠን አንድ ሰዉ በላቡ እና በጥረቱ ወይም በሌላ ህጋዊ መንገድ ባገኘዉ የንብረት ባለቤትነት መብቱ ተጠቃሚ እንዲሆን፣ በሌላ በኩል ሌላ ሰዉ የእራሱ ባልሆነዉ ወይም በሌላ ሰዉ ንብረት ያላግባብ ተጠቃሚ እንዳይሆን በማድረግ ከንብረት ባለቤትነት መብት ጋር በተያያዘ ያለዉን የፍትሕ ሚዛን የመጠበቅ ኃላፊነት አለባቸዉ፡፡

ይህ ከላይ የተመለከተዉ አጠቃላይ መርህ ከፍቺ በኋላ ከንብረት ክፍፍል ጋር በተያያዘ በባልና ሚስት መካከል በሚነሳ ክርክር ላይም እንደአግባብነቱ ተፈፃሚ ሊሆን እንደሚገባም እሙን ነዉ፡፡ ባልና ሚስት ጋብቻቸዉን በሚፈጽሙበት ጊዜ በየግል የነበሯቸዉ ንብረቶች ወይም ከጋብቻ በኋላ በዉርስ ወይም በስጦታ በየግላቸዉ ያገኙዋቸዉ ንብረቶች የግል ንብረቶቻቸዉ ሆኖ እንደሚቀሩ፣ በጋብቻ በሚኖሩበት ወቅት ከግል ጥረታቸዉና ከግል ወይም ከጋራ ንብረታቸዉ የሚያገኟቸዉ ገቢዎች ሁሉ የጋራ ሀብቶቻቸዉ እንደሚሆኑ፣ የግል ይባልልኝ የሚል አቤቱታ ቀርቦ በፍርድ ቤት የጸደቀ እንደሆነ ባልና ሚስት ከተጋቡ

ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በኋላ አንዱ የግል ሀብቱ በሆነ ንብረት ለዉጥ ያገኘዉ ወይም በግል ገንዘብ የገዛቸዉ ወይም የግል ንብረቱን ሸጦ የሚያገኘዉ ገንዘብ የግል ሀብቱ እንደሚሆን እንዲሁም የባልና ሚስት የጋራ ሀብት ለሁለቱም ተጋቢዎች እኩል እንደሚከፋፈል በፌዴራል የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 57፣ 58፣ 62(1) እና 90 ላይ የተመለከቱት ድንጋጌዎችም ይህንኑ የሚያሳዩ ናቸዉ፡፡ ከዚህ የምንረዳዉ ከባልና ሚስት አንደኛዉ ተጋቢ በሌላኛዉ ተጋቢ ንብረት ያላግባብ እንዲበለጽግ ወይም ከጋብቻ በፊት አንደኛዉ ወገን በግል ጥረቱ ባፈራዉ ንብረት ላይ ያለዉ የባለቤትነት መብት ያላግባብ እንዲገደብ የቤተሰብ ህጉ የማይፈቅድ መሆኑን ነዉ፡፡

ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ፣ ከፍ ሲል እንደተገለጸዉ፣ ለዚህ ሰበር ክርክር መነሻ የሆነዉ ቤት አመልካች ከተጠሪዎች አባት ጋር ጋብቻ ከመመስረታቸዉ በፊት በ1988 ዓ.ም ከሌላ ሰዉ የገዙ ስለመሆኑ ተጠሪዎች ክደዉ አልተከራከሩም፡፡ ከጋብቻ በፊት የተፈራ ንብረት ደግሞ የተጋቢዉ የግል ሀብት ሲሆን፣ የባልና ሚስት የጋራ ንብረት ሊሆን የሚችለዉ በገዛ ፈቃዳቸዉ በሚያደርጉት የጋብቻ ዉል የጋራቸዉ እንዲሆን የተስማሙ እንደሆነ ብቻ ስለመሆኑ በቤተሰብ ህጉ አንቀጽ 42፣ 57 እና 85 ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ በተያዘዉ ጉዳይ አመልካች ከተጠሪዎች አባት ጋር ጋብቻ ከመመስረታቸዉ በፊት ያፈሩትን ለዚህ ሰበር ክርክር መነሻ የሆነዉን ቤት የጋራ ለማድረግ በጋብቻ ዉል የተስማሙ ስለመሆኑ የቀረበ ክርክርም ሆነ ማስረጃ የለም፡፡ ስለሆነም ቤቱን የባልና ሚስት የጋራ ሀብት ሊያደርግ የሚችል ከዉል ወይም ከህግ የመነጨ ምክንያት የለም፡፡ ከላይ እንደተመለከተዉ፣ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነት ማረጋገጫ ማስረጃ (የምስክር ወረቀት)፣ አንድ ሰዉ በአንድ ንብረት ላይ ያለዉን መብት ለማረጋገጥ ሲባል በማስረጃነት የሚሰጥ እንጂ በእራሱ መብትን የሚፈጥር ባለመሆኑ፣ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ንብረት የአመልካች እና የሟች ባለቤታቸዉ (የተጠሪዎች አባት) የጋራ ሊያደርግ የሚችል ህጋዊ ምክንያት በሌለበት ሁኔታ፣ የሟች ስም በማስረጃዉ ላይ መጠቀሱ ብቻ ንብረቱን የጋራ አያደርገዉም፡፡ የማይንቀሳቀስ ንብረትን አስመልክቶ በሚመለከተዉ የአስተዳደር አካል የሚሰጠዉ የባለቤትነት ማረጋገጫ ማስረጃ በክርክር ሂደት የሚኖረዉን ዋጋ እንዲሁም ማስረጃዉን ማስተባበል የሚቻልበት ሁኔታን አስመልክቶ በፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 1195 እና 1196 ላይ የተመለከቱት ድንጋጌዎች አተገባበርም ይህንኑ ባገናዘበ መልኩ ሊሆን ይገባል፡፡ በመሆኑም፣ የተጠሪዎች አባት የንብረቱ ተጋሪ ሊሆን የሚችልበት ህጋዊ ምክንያት በሌለበት ሁኔታ፣ ስማቸዉ በባለቤትነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ላይ መመዝገቡን ብቻ መሠረት በማድረግ፣ የቤቱ ግማሽ ድርሻ የተጠሪዎች ነዉ በሚል በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የጸና ዉሳኔ ሊታረም የሚገባዉ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 5 የቤት ቁጥር 173 ከሆነዉ ንግድ ቤት ጋር በተያያዘ አመልካች ያቀረቡትን ቅሬታ ስንመለከት፣ ቤቱ የተሰራዉ ጋብቻ ከመመስረቱ በፊት በሟች (የተጠሪዎች አባት) ስለመሆኑ አመልካችም ክደዉ አይከራከሩም፡፡ ይህ ቤት የጋራቸዉ እንዲሆን በጋብቻ ዉል የተስማሙ ስለመሆኑ አልተረጋገጠም፡፡ ከሟች ጋር በጋራ በመሆን ቤቱን ማከራየታቸዉ አመልካችን የቤቱ ተጋሪ አያደርጋቸዉም፡፡ በመሆኑም አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረቡትን ክርክር ዉድቅ በማድረግ የተሰጠ ዉሳኔ፣ በአግባቡ ነዉ ከሚባል በስተቀር ሊነቀፍ የሚችልበት ህጋዊ ምክንያት የለም፡፡

በዚህ ሁሉ ምክንያት ተከታዩ ተወስኗል፡፡

**<u>ዉሳኔ</u>**

*ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 112478ላይ መስከረም 21ቀን 2014 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 282131 ላይ ሐምሌ19 ቀን 2014ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 348(1) መሠረት ተሻሽለዋል፡፡

2. በአዲስ አበባ ከተማ ኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ ወረዳ 02 የቤት ቁጥር አዲስ፣ የካርታ ቁጥር ወ2/ዉዝ01/1510/24129/00 የሆነዉን ቤት አስመልክቶ የተሰጠዉ የዉሳኔ ክፍል ተሸሯል፤ ቤቱም የአመልካች የግል ሀብት በመሆኑ ተጠሪዎች ከቤቱ ድርሻ የላቸዉም ተብሎ ተወስኗል፡፡

3. በተራ ቁጥር 2 ላይ ከተገለጸዉ ዉጪ ያለዉ ቀሪዉ የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ክፍል አልተነካም፡፡

4. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/ተ

*ማ ስታወሻ፦ ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*